

*From Oblivion to Memory*

ልዩ እትም ቁጥር 1

# የካቲት 12

**የሕዝብ ጭፍጨፋና የጅምላ እስር**

## ከዝግጅት ክፍላችን

የካቲት 12 ቀን በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ታላቅ ተፅዕኖ ያለው ቀን ነው። በኢትዮጵያ አቆጣጠር ከ 1928 እስከ 1933 ድረስ ባለው ግዜ ውስጥ በፋሺስት ኢጣልያ ታፍነው ተወስደው በእስር ሲማቅቁ የነበሩ እናትና አባቶች፣ አያቶችና፣ ቅድም አያቶች ተወላጅና ቤተሰብ የሆንን ሰዎች የዚህን ቀን ታሪክ ታላቅነት በመገንዘብ በዓለም ደረጃ **እንዲዘከር** ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ እንዳለብን ተገንዝበን፣ የድርጅታችንን የመጀመሪያውን ልዩ እትም ጦማር ስናቀርብላችሁ በኩራት ነው። በዚህ እትም፣ ፋሺዝምን እምቢኝ ብለው ላገራቸው አንድነትና ነፃነት ሲሉ ብዙ ዋጋ የከፈሉና ለእንግልት፣ ለእስርና ሕይወትን ለማጣት የበቁ ወገኖቻችን ታሪክ ተዳፍኖ መቅረቱን በማስተዋልና ስማቸውን ለማስጠራት ቁርጠኛ ሁነን በመነሳት የየካቲት 12ን ጭፍጨፋ ዘግበን አቅርበናል። በዚህ መታሰቢያ የተዳፈነው እንዲዘከር ኃላፊነታችንን በመወጣት የምናቀርበው ፅሑፍ ግፉ የተፈፀመበትን ቀን መድረስ በማሰብ ነው። ይህን ታሪካዊ ክስተት በዚህ መነሻችን በሆነው ጦማር ስናቀርብላችሁ የዕለቱን ሰቆቃ በአጭሩ ለማስታወስና የፋሽዝም የግፍ አገዛዝና የቅኝ ግዛት መርሕ እንዴት አድርጎ አንድ ሕዝብን ከነታሪኩ ጨፍልቆ እውቀቱን፣ ታሪኩንና ድምፁን እንዲያጣ ለማድረግ እንደሞከረ ለማሳየት ነው።

## በቀልና ቅኝ ግዛት እንደ መንስዔ

ከቅኝ ገዥነትና የበቀል ስሜት የተፀነሰው የ1889 የኢጣልያ ወታደራዊ ዘመቻ አድዋ ላይ በኢትዮጵያ ወሳኝ ድል መታቀቡ ይታወሳል። ይህ ኢትዮጵያ በኢጣልያ ላይ የተጎናፀፈችው ዳግም ድል[1] ያመረቀዘው የበቀል ስሜት ኢጣልያን አልለቀቃትም ነበርና ሙሶሊኒ በ1923 ጦሩን ወደ ኢትዮጵያ ባዘመተበት ወቅት ድርብ ዓላማ ነበረው። አንዱ የኢጣልያን ቅኝ ግዛት ማስፋፋት ሲሆን ሌላው ደግሞ ኢጣልያን መበቀል ነበር። ይህንንም ለሕዝቡ ሲያቀርብ ባለፈው ኢጣልያ ለመዋረዷ ፋሺዝም ምላሽ እንደሚሆን አድርጎ ነበር። በሰሜን በኤርትራ በኩል፣ በደቡብ ምሥራቅ በሶማልያ በኩል የዘመተውን የኢጣልያ ጦር ለመከላከል በኢትዮጵያውያን በኩል የተደረገው መረባረብ ከባድ ቢሆንም የኢጣልያ ዘመናዊ መሣሪያዎች[2] አይለው አዲስ አበባ በ1923 በኢጣልያ ኃይል ሥር ወደቀች።

[1] የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ድል በጥር 18 1879 ዶግዓሊ ላይ እንደነበረ ልብ ይሏል።
[2] ኢጣልያ ከተጠቀመችባቸው መሣሪያዎች መካከል የአየር ድብደባና የኬሚካል ጭሶች ይገኙበታል።



**የየካቲት 12 መታሰቢያ የሰማዕታት ሐውልት**

## የነጭ የበላይነትና የግፍ አገዛዝ

የኢጣልያ መንግሥት አዲስ አገዛዝ መሠረት የነበረው የዘር መድልዖና የአፈና ሥርዓት አዲስ አበባ ላይ ሰፈነ። ኢጣልያ የነጭ የበላይነትን መርሕ ያደረገ ሥርዓት አስርፃ ኢትዮጵያ የኢጣልያ ምሥራቅ አፍሪካ ግዛት አካል መሆኗን በማወጅ ግራዚያኒን ገዥ አድርጋ ላከች። ሮዶልፎ ግራዚያኒ ከዚያ ቀደም ብሎ ሊብያ በነበረበት ግዜ በጭካኔው ስም የተከለና[1] ከዚያም ሶማልያ በነበረበት ግዜ በጅምላ ፍርድና በጭካኔው የሚታወቅ ነበር። በኢጣልያ አገዛዝ ኢትዮጵያውያን የበታች ሆነው በፍርሃት እንዲኖሩ ተደረገ። ግራዚያኒ “ኢትዮጵያውያን ቢኖሩም ባይኖሩም” ኢትዮጵያ የሙሶሊኒ እንደምትሆን ቃል በመግባት ጭካኔ የተሞላበትን አገዛዝ በመቀጠል የኢትዮጵያውያንን የነፃነት ተጋድሎ የመግታት ጥረቱን አፋፋመ። የኢጣልያ መንግሥት ተፅዕኖ በጉልህ ይታይ የነበረው በከተማዎች ሲሆን፣ ከከተማዎች ራቅ ሲል የአርበኞች እንቅስቃሴ ያይል ነበር። የግራዚያኒ ትኩረት የነበረው አገር ማስተዳደር ላይ ሳይሆን የአርበኞችን እንቅስቃሴ መደፍጠጥና ማፈን ላይ ነበር።

[1] ግራዚያኒ በሊብያ ከፈፀማቸው ግፎች በመነሳት፣ “የፌዛኑ አራጅ” የሚል ስያሜ ተሰጥቶት ነበር።

## ጭፍጨፋና ሰቆቃ



የካቲት 12 ቀን 1923 በአዲስ አበባ ከተማ አብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስገደም ቤተመንግሥት ግቢ ውስጥ ሕዝብ በተሰበሰበበት ግራዚያኒ ላይ ባደረጉት የቦምብ ጥቃት ግራዚያኒና ሌሎች የመቁሰል አደጋ ሲደርስባቸው አንድ ሰው ሕይወቱን አጣ። ጣሊያኖቹ አላመነቱም። ወዲያውኑ ተዋጊ ለሆኑም ላልሆኑም የጣልያን ተወላጆች በወጣ መመሪያ መሠረት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ እንዲገደል ወታደርና ሲቪል ኢጣልያዊ፣ እንዲሁም አስካሪዎች[1] ተባብረው ኢትዮጵያውያን ላይ ሦስት ቀን ሙሉ ባደረሱት ከባድ ጭፍጨፋ በሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ዘግናኝ በሆነ ሁኔታ ተጨፍጭፈው በየመንገዱም፣ በየቤታቸውም አለቁ። መኖሪያ ቤቶች ሰዎች ውስጣቸው እንደተቀመጡ በእሳት ጋዩ። ታሪክንም ሆነ እውቀትና ማንነትን ለማጥፋት በታሰበ መልኩ ውጭ ተምረው ተመልሰው አገራቸውን ያገለግሉ የነበሩ ኢትዮጵያውያን፣ ልሂቃንና ባለሙያዎች ተለቅመው ተጨፈጨፉ። እሱ ላይ ሙከራ ያደረጉት ሰዎች ወደዚያ ሸሽተዋል የሚል ወሬ የሰማው ግራዚያኒ በደብረ ሊባኖስ ገዳም የሚገኙ መነኮሳትም ሆነ ማንኛውም ሰው እንዲገደል ባዘዘው መሠረት አንድም ሰው እንዳይተርፍ ተደረገ።

[1]የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ድል በጥር 18 1879 ዶግዓሊ ላይ እንደነበረ ልብ ይሏል።

[2]ኢጣልያ ከተጠቀመችባቸው መሣሪያዎች መካከል የአየር ድብደባና የኬሚካል ጭሶች ይገኙበታል።

### ከአዲስአበባ ሕዝብሩብ ያህሉበግፍ ተጨፍጭፎተገደለ። በየደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ሃማኖት ገዳም የሚገኙ *298* መናንያንመነኮሳት፣ ካህናትናሌሎችም አንድሰው በሕይወት እንዳይቀርተደርጎ ተጨፈጨፉ።

**አፈና፣ ግዞትና እስር** ከዚህ ሁሉ ጭፍጨፋና እልቂት በኋላ ጣልያኖች ኢትዮጵያውያን ላይ የሚያደርጉትን ክትትልና የጅምላ ፍርድ አጥብቀው ቀጥለው ዳናኔና ኦጋዴን፣ እንዲሁም ሌሎች መሰል ቦታዎች ላይ እስረኞችና ምርኮኞችን አስረው አሰነበቱ። ከአራት መቶ በላይ የሆኑ መኳንንት፣ ባለሥልጣናት፣ አርበኞችና ተፅዕኖ ፈጣሪዎች እንዲሁም የቤተሰቦቻቸው አባላት ታፍነው ወደ አዚናራ ደሴት ተወስደው፣ ብዙ ሰዎች ሕይወታቸው በዚያው አልፏል።

ይህ የታሪካችን አካል ክብደቱን የሚመጥን ዕውቅና አልተሰጠውም። የአገርን አንድነትና ነፃነት ለማስጠበቅ ለሚደረገው ተጋድሎ መስዋዕት የከፈሉና አካላዊም ሆነ መንፈሳዊ ጉዳት የደረሰባቸው፣ የታሰሩ፣ የተፈናቀሉና የታጎሩ መዘንጋት የለባቸውም። የየካቲት 12 ጭፍጨፋ ታሪክ አግባቡ የሚሆን ቦታ ማግኘት ይገባዋል። ይህን ጭፍጨፋ ያስፈፀመው ግራዚያኒ በተወለደበት ከተማ በ2004 ሐውልት ተሠርቶለት የተዘከረ ቢሆንም የካቲት አስራ ሁለት የጥቁር ሰዎች የእምቢተኝነትና የፅናት ተምሳሌት ሆኖ የሚከበረው ጥቂትና የተወሰኑ ዝግጅቶች ላይ ብቻ ነው።



[1] አስካሪዎች በየግዛቱ ተመልምለው የአውሮፓውያን ቅኝ ገዥዎች የደህንነት ሥራ የሚፈፅሙ ያገሩ ተወላጆች ናቸው።

**ድርጅታችን** ለኛም፣ ለትውልድም የተሻለ ታሪክ ለመፍጠርና ነፃነታችንን አስከብረን ወደፊታችንን ብሩህ ለማድረግ ያለፈውን ታሪካችንን እውቅና በመስጠት፣ ለነፃነት ሲባል በተደረገው ተጋድሎ ወገን ላይ የደረሰውን በደል በመገንዘብና በመዘከር እኛም ዛሬ የነሱን ሥቃይና ድካም ልብ እንድንል ያሳስባል።